ልክ እንደ 1፣ 2፣ 3 ቀላል ነው!

# የእርስዎን Medicaid ወይም MCHP ሽፋን መጠቀም

## 1 የ Medicaid ካርድዎን ይያዙ እና Managed Care Organization (MCO, ተያያዥ እንክብካቤ የሚሰጥ ድርጅት) ይምረጡ

**Medicaid ካርድዎን ያስቀምጡ።** በተመዘገቡ በ 14 ቀናት ውስጥ ቀይ ወረቀት እና ነጭ ካርድ በፖስታ ይደርሰዎታል። ይህንን ካርድ እንዳይጥሉ። እስካሁን ድረስ ካርድዎን ያልተቀበሉ ቢሆንም፣ የ Medicaid መታወቂያዎን በመጠቀም አሁንም የህክምና አገልግሎቶችን ማግኘት ይችላሉ።

ማመልከቻዎ የተሟላ እና የተረጋገጠ ከሆነ፣ የእርስዎን ህክምና እንዲሰጥ MCO ይመርጣሉ።

**ዶክተርዎ የሚቀበለውን MCO ይመልከቱ።** የትኛውን MCO እንደሚወስዱ ለመጠየቅ በቀጥታ ወደ ዶክተርዎ መደወል ይችላሉ፣ ወይም የእርስዎን MCO ለሚቀበሉ ዶክተሮች በ **MarylandHealthConnection.gov/find-a-provider** ላይ መፈለግ ይችላሉ።

**የእርስዎን ህክምና እንዲሰጥ MCO ይመርጣሉ።** የመረጡት ሐኪም የሚቀበለውን MCO ይምረጡ። እርስዎ MCOን ካልመረጡ፣ ግዛቱ አንዱን ይመርጥልዎታል።

ከእነዚህ መንገዶች በማናቸውም መመዝገብ ይችላሉ፡-

1. **MarylandHealthConnection.gov** ን ይጎብኙ እና ወደ አካውንትዎ ይግቡ
2. ነፃ የሞባይል መተግበሪያችንን ያውርዱ፣ MHC ይመዝገቡ
3. በ **1-855-642-8572** ይደውሉልን። **መስማት የተሳናቸው እና መስማት የማይችሉ በመልእክት ማሰራጫው አገልግሎት ይጠቀሙ።**
4. የመመዝገቢያ ኪት በፖስታ እንዲላክልዎ ይጠይቁ (በኦንላይን አካውንትዎ ላይ ወይም ለእኛ በመደወል ማድረግ ይችላሉ።)

እርስዎ ሊመርጧቸው የሚችሏቸው MCOs:-

- Aetna Better Health of Maryland
- Wellpoint Maryland
- Jai Medical Systems
- Kaiser Permanente
- Maryland Physicians Care
- MedStar Family Choice
- Priority Partners
- UnitedHealthcare
- CareFirst BlueCross BlueShield Community Health Plan of Maryland (CareFirst CHPMD)

## 2 የእርስዎን ሽፋን መረዳት

የእርስዎ **MCO** እነዚህን እና ሌሎች አገልግሎቶችን ይሸፍናል፡-

- ሄዶ በሃኪም መታየት፣ መደበኛ ምርመራዎችን እና ስፔሻሊስቶችን ጨምሮ
- የእርግዝና እንክብካቤ
- የቤተሰብ ምጣኔ እና የወሊድ መከላከያ



© 2023 Maryland Health Benefit Exchange | MHC018_092023_AM

**Maryland Children's Health Program (MCHP፣ የሜሪላንድ የልጆች ጤና ፕሮግራም) እስከ 19 አመት ለሆኑ ልጆች ሙሉ የጤና ጥቅማጥቅሞችን ይሰጣል። ለልጆች የሚሰጠው ጥቅማጥቅሞች የሚከተሉትን እና ሌሎችንም ያጠቃልላል:-**

- ሄዶ በሀኪም መታየት (ጤንነት እና የህመም እንክብካቤ)
- የላብራቶሪ ስራ እና ምርመራዎች
- የእይታ እንክብካቤ
- ክትባቶች (መርፌዎች)
- በሐኪም የታዘዙ መድኃኒቶች
- የሆስፒታል እና የድንገተኛ አገልግሎቶች
- የመጀመሪያ ደረጃ የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች በዶክተርዎ አማካኝነት
- የጥርስ እንክብካቤ በ **Maryland Healthy Smiles Dental Program (ጤናማ ፈገግታዎች የጥርስ ፕሮግራም)**

## 3 Medicaid ወይም MCHPን የሚቀበል ዶክተር መፈለግ

**በእቅድዎ ውስጥ ያለ ሐኪም ይፈልጉ።** በ **MarylandHealthConnection.gov/find-a-provider** ላይ በኦንላይን ላይ ይፈልጉ እና የእርስዎን MCO መቀበላቸውን እርግጠኛ ለመሆን ወደ ዶክተርዎ ቢሮ ይደውሉ።

**ቀጠሮ ያስይዙ።** የዶክተር ቀጠሮ ሲያዚዙ፣ እርስዎ በ Medicaid ወይም MCHP ውስጥ መመዝገብዎን ያሳውቋቸው እና የእርስዎን MCO ስም ይስጧቸው።

**ለመጀመሪያ ቀጠሮዎ ይዘጋጁ።** ዶክተር ካገኙ እና የመጀመሪያ ቀጠሮዎን ካስያዙ በኋላ፣ የሚከተሉትን ይዘው ይምጡ:-

- ቀይ እና ነጭ የህክምና እርዳታ ካርድ እና የ MCO ካርድዎ
- በአሁኑ ጊዜ የሚወስዷቸው የማንኛውም መድሃኒቶች ዝርዝር

## በቤተሰብዎ ወይም በገቢዎ ላይ ስለሚደረጉ ለውጦች ይንገሩን

ከተመዘገቡ በኋላ፣ ትክክለኛውን ሽፋን እና የገንዘብ ድጋፍ እያገኙ መሆንዎን ለማረጋገጥ በቤተሰብዎ ወይም በገቢዎ ላይ ለውጦች ካሉ ለ Maryland Health Connection ወዲያውኑ ማሳወቅ አስፈላጊ ነው።

የኦንላይን መተግበሪያዎን ያዘምኑ፣ በ **1-855-642-8572 ይደውሉልን (መስማት የተሳናቸው እና መስማት የማይችሉ በመልእክት ማሰራጫው አገልግሎት ይጠቀሙ)**፣ ወይም በ **MarylandHealthConnection.gov/help** ላይ በነጻ፣ በአካል እገዛ ያግኙ።

ሪፖርት ማድረግ ያለብዎት ለውጦች የሚከተሉትን ያካትታሉ:-

- ጋብቻ ወይም ፍቺ ሲፈፀሙ
- ልጅ መውለድ፣ ልጅ በማደጎ ማሳደግ ወይም ልጅን በጉዲፈቻ ወይም ለማደጎ ማሳደጊያ መስጠት
- በገቢ ላይ ለውጦች
- ወደ ሜሪላንድ መቀየር እና በ ግዛት ውስጥ ቤት መቀየር
- በአካል ጉዳተኝነት ሁኔታ ላይ ለውጥ ካለ
- ጥገኞች ሲኖሯችሁ ወይም ሲሄዱ
- ሌሎች አንዳንድ የጤና ሽፋን ኪሳራዎች (ቀጣሪያችሁ ሽፋንን ሲያቋርጥ፣ ስራ ማጣት ወይም ሽፋን የሚሰጥ ስራን መተው ያሉ)
- 26 አመት ሲሞላ እና ከወላጅዎ የጤና እቅድ መውጣት

እንዲሁም በብቁነትዎ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳርፉ የማይችሉ ሌሎች ለውጦችን ሪፖርት ማድረግ አለብዎት፣ ለምሳሌ በአድራሻዎ ላይ የተደረጉ ለውጦች እና በስምዎ፣ በትውልድ ቀንዎ ወይም በሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥርዎ ላይ እርማቶች ካሉ። በ **MarylandHealthConnection.gov/after-you-enroll/report-changes/** ላይ የበለጠ ይማሩ።



© 2023 Maryland Health Benefit Exchange | MHC018_092023_AM